Washington State Department of Health

# የመኒንንኮካል እና የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV)

ውድ ወላጆች/አሳዳጊዎች፤

ወላጅ እንደመሆንዎ መጠን የልጅዎን ጤንነት እንደማስጠበቅ ያለ ኣስፈላጊ ሌላ ነገር የለም። የዋሽንግተን ስቴት ሕግ ኣስከባሪ ስለ ሜኒንንኮካል ስለተባል በሽታ እና ስለ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ፣ ኣንዳንድ ጭብጦች ስለነዚህ በሽታዎች እና ስላለ ልጅዎን ለመከላከል የሚያስችል ክትባት የሚመለከት መረጃ እንድንሰጣችሁ ይጠይቀናል።

## ሜኒንንኮካል በሽታ እና መከላከያው

### የሜኒንንኮካል በሽታ ምንድን ነው?

የሜኒንንኮካል በሽታ ኣደገኛ የባክቴሪያ ጥቃት (ኢንፌክሽን) ነው። እንደ እድል ሆኖ ይህ ለሂወት ያሚያሰጋ በሽታ ኣሳቻ ነው ያሚያጋጥመው። በዋሽንግተን ስቴት በዓመት ውስጥ ከ20 እስከ 50 የተጠቁ ሰዎች ብቻ ያጋጥማል። በጣም የተለመዱት የበሽታው ምልክቶች እንደ ትኩሳት፣ ሳል፣ ራስምታት እና የቆዳ ማስከክ የመሳሰሉት ናቸው። ይህ በሽታ ሜኒንጃይተስ (የእንንል እና የጀርባ ነርብ መሸፈን) ሊያስከትል ይችላል። ይህ በሽታ በበሽታው ከተጠቃ ሰው ጋር በመቀራረብ ሊተላለፍ ይችላል። ታዳጊዎች እና ወጣቶች በተለይ በጋር የትማሪዎች ማረፊያ ውስጥ  የሚኖሩ ከሆኑ ለሜኒንንኮካል በሽታ የተጋለጡ ናቸው።

### ልጄን እንዴት ከሜኒንንኮካል በሽታ መከላከል እችላለሁ?

የሜኒንንኮካል ክትባት ወይም MCV4 ኣራት የተለያዩ ዓይነት በሽታዎችን ይከላከላል። ሁሉም ዕድሜያቸው ከ 11 ኣስከ 12 ዓመት የሆነ ህጻናት ክትባቱን ቢወስዱ ይመረጣል። ክትባቱ ለሁለተኛ ግዜ ዕድሜያቸው 16 እስከ 18 ዓመት ሲሆናቸው ይሰጣል።

### የሜኒንንኮካል ክትባት የት ኣገኛለሁ?

ስለ በሽታው የበለጠ ለመማር ሓኪማችሁን፣ ነርስ ወይም ባካባቢያችሁ ያለ የጤና ጣቢያ ኣነጋግሩ። የዋሽንግተን ስቴት ዕድሜያቸው እስከ 18 ዓመት ለሆኑ ህጻናት እና ታዳጊዎች ነጻ ክትባት ይሰጣል። ክትባቱን የሚያቀርቡ ኣገልግሎት ሰጪዎች ያገልግሎት መተነኛ ክፍያ ያስከፍሉ ይሆናል። ይህን ክፍያ መክፈል የማይችሉ ስዎች ይህ ክፍያ እንዲሰረዝላቸው መጠየቅ ይችላል።

### ስለ ሜኒንንኮካል በሽታ እና መከላከያው የበለጠ መረጃ ማግኘት ከፈልጋችሁ፤

- የዋሽንግተን ስቴት ዲፓትመንት ኦፍ ሄልዝ (የዋሽንግተን ስቴት የጤና ክፍል)
  www.doh.wa.gov/YouandYourFamily/Immunization/Diseases/MeningitisMeningococcalDisease.aspx
- ሴንተር ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል ኤንድ ፕሪቬንሽን (የበሽታ መከላከያ እና ቁጥጥር ማእከል)
  www.cdc.gov/vaccines/hcp/vis/vis-statements/mening.html
- ቺልድረንስ ሆስፒታል ኦፍ ፊላደልፊያ ቫክሲን ኢዱኬሽን ሴንተር
  http://prod-www.chop.edu/conditions-diseases/meningococcal-infections

## ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) እና መከላከያው

### ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) ምንድን ነው?

ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) የተለመደ ዓይነት ቫይረስ ነው። ብዙ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ጋር ንክኪ ያደረጉ ሰዎች በበሽታው ኣይጠቁም። ሆኖም ግን ለኣንዳንድ ሰዎች ኣደገኛ የሆነ የጤና ችግር እንደ የማህጸን፣ የፊንጢጣ፣ የኣፍ እና የጉሮሮ ካንሰር ሊያስከትል ይችላል። ብዙ የተጠቁ ሰዎች ምንም ዓይነት ምልከት ኣያስዩም። ሳይገባቸው በሽታውን ሊያሰራጩ ይችላሉ። ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ዋና መተላለፊያው ጾታዊ ግንኙነት ነው።

### ልጄን እንዴት ከሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) በሽታ መከላከል እችላለሁ?

ልጅዎ የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባት ማግኘቱን ኣረጋግጡ። ክትባቱ በጣም ፍቱን ነው። <u>ክትባቱ ለማግኘት ጥሩ ግዜ የሆነ የጾታዊ ተግባር ከመጀመር በፊታ ያሉ ዓመታት ይመረጣሉ</u>። የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባት ማግኘት በጣም ከተለመዱት እና ኣደገኛ ከሆኑት ካንሰር እና የቭልት ቁስል ልያስከትሉ ከሚችሉት የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ዓይነቶች ይከላከልላል። ክትባቱ የተጠቃን ሰው ኣያድንም።

### የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) ክትባት ማግኘት ያለበት ማን ነው? መቼስ ሊሰጣቸው ይገባል?

ለሂሉም ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 12 ዓመት የሆነ ሴቶች እና ወንዶች ሶስት የተለያየ መጠን የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባት ቢያገኙ ይመረጣል። ለሴቶ እስከ 26 ዓመት ለወንዶች እስከ 21 ዓመት ባለ ግዜ ቢወስዱት ይመረጣል። ከሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ክትባት በተጨማሪ ከ11 እስከ 12 ዓመት ያሉ ልጆቻችሁ የTdap እና የሜኒንንኮካል ክትባት ቢሰታቸው ይመረጣል።

### የሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) ክትባት የት ማግኘት እችላለሁ?

ሓኪማችሁን፣ ነርስ ወይም ባካባቢያችሁ ያለ የጤና ጣቢያ ስለክትባቱ ጠይቁ። በተጨማሪም የት እንደሚሰጥ ጥይቁ።

### ስለ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV)፣ ክትባት እና የማሕጸን ካንሰር የበለተ መረጃ ለማግኘት፤

- የዋሽንግተን ስቴት ዲፓትመንት ኦፍ ሄልዝ (የዋሽንግተን ስቴት የጤና ክፍል)
  www.doh.wa.gov/Portals/1/Documents/Pubs/348-187_HumanPapillomavirusVaccineFactsheet.pdf
- ሴንተር ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል ኤንድ ፕሪቬንሽን (የበሽታ
  መከላከያ እና ቁጥጥር ማእከል) www.cdc.gov/std/hpv/
- የኣሜሪካን ካንሰር ሶሳይቲ (የኣሜሪካ
  የካንሰር ማሕበረሰብ)
  www.cancer.org

ከብዙ ትሕትና ጋር፤

Student Health Services, Seattle Public Schools